# አብዮታዊት ኢትዮጵያ ②

★ የትግል ፕሮግራም

★ ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ

★ ወዝ አደርና ፓርቲው

★ ሌኒንዝም ምንድን ነው ?

ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

ርእሰ አንቀጽ ።

# የትግል ፕሮግራም

የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች በርሀብ ፣ በድንቁርናና በበሽታ እውተብትቦ ሲያሠቃያቸው የቆየው ጨለማው የፊውዳል አገዛዝ እነሆ በዓይናችን ሥር እየተፍረከረከና እየፈራረሰ ሲሔድ እናያለን ይህን አረመኔ ሥርዓት ከኢምፔሪያሊስቶች አጋሮቹ ጋር ደምስሶ አዲስ ሕዝባዊት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የሚደረገው ታሪካዊ ተጋድሎ ለአድኃሪ ኃይሎች ምንም ዓይነት ፋታ ሳይሰጥ ወደፊት መገስገስ ይኖርበታል ። በዚህ ትግል ውስጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጠላቶች ሙሉ በሙሉ ሊያንበረክክና በጭቁኖች ላብ ደምና እንባ ላይ የተገነባውን ግፈኛ ሥርዓታቸውን በማያዳግም ሁኔታ ሊደመስስ የሚችለው ኃይል የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረ ክንድ ብቻ ነው ።

አንዴ እየቀዘቀዘ አንዴ እየተፋፋመ ምንጊዜም ያለማቋረጥ የኢትዮጵያ ጭቁኖች በመሥዋዕትነት የጻፉት አኩሪ የትግል ታሪክ በየካቲት ከፈነዳ ወዲህ የትግሉ ሰደድ አገሪቱን ከማጥለቅለቅ ያቋረጠበት ጊዜ የለም ። ከየካቲት ወዲህ በተደረገው ትግል የኢትዮጵያ ጭቁኖች ብዙ የማይናቁ ድሎችን አግኝተዋል ። ነገር ግን በተነጥላ የተወሰዱ ታላላቅና አብዮታዊ ርምጃዎች ቢኖሩም እስከ ዛሬ ድረስ የአብዮታችን ጠባይና ጠቅላላ አቅጣጫ ፣ የቅርብ ጊዜና የሩቅ ጊዜ ዓላማ ጥርት ባለ ሁኔታ አልቀረቡም ነበር ። በዚህም የተነሣ የአብዮቱ ቁርጠኛ ወዳጆችና ጠላቶች በሚገባ በሳይንሳዊ ትንተና ተጠቁመው የሚታወቁበት ሁኔታ አልነበረም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ትግሉ ግቡን ሊመታ የሚችልበት ሳይንሳዊ የአብዮት ፋና ጥርት ባለና በሚያስተማምን ሁኔታ አልተተለመም ነበር።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በመንግሥት ደረጃ መታወጅ ለነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ሳይንሳዊ የሆኑ ፍቱን መልሶችን የሚያበሥር አብዮታዊ ድርጊት ነው ። ስለሆነም፣ እንደማንኛውም አብዮታዊ ድል ይህ ፕሮግራም መላ የኢትዮጵያ ተራማጆች በግንባር ቀደምትነት የተዋጉበት የሰፊው ሕዝብ መራራ ትግል ውጤት ነው ።

የኢትዮጵያ ተራማጆች በይዘቱ ይህንን በመሰለ ፕሮግራም ሥር ተሰልፈው ለመታገል የጀመሩት በሚያዝያ ወር ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. አይደለም ። በአብዮታችን ትግል በግንባር ቀደምትነት የተሰውት የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ሰንደቅ ዓላማ ሥር ሆነ ብለው ሲታገሉ ብዙ ዓመታት አልፏቸዋል ። ከተማሪዎችም ንቅናቄ ውጪ የኢትዮጵያ ተራማጆች ጥራት ባለው የትግል ፕሮግራም ተደራጅተው በታገሉበት ጊዜ ሁሉ ይህ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሰብሰቢያ ዓላማቸው መሆኑን እስካሁን በይፋ ሕልውናቸውን ያበሠሩ ድርጅቶች በሙሉ አሳይተዋል ። ስለሆነም ይህ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ትናንት ግንባር ቀደም ተማሪዎች ተሰልፈው የተዋጉበትና የተሠውበት ፣ ዛሬ ደግሞ የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ በድርጅት፣ በቡድን ፣ በግለሰብ ደረጃ ተሰልፈው የሚታገሉለት አብዮታዊ ፕሮግራም ነው ።

እርግጥ ይህ ፕሮግራም በይዘቱ ከዚህ ቀደም በተማሪ ንቅናቄዎች ከተነደፉ ፕሮግራሞች ፣ ዛሬም የኢትዮጵያ ተራማጆች ነድፈው ትግሉን ለመሰብሰብ ለማስተባበርና አቅጣጫ ለመስጠት በይፋ ከገለጧቸው ፕሮግራሞች ጋር ሙሉ በሙሉ ላይመሳሰል ይችላል ። ከዛሬይቱ በአብዮት ማዕበል በመጥለቅለቅ ላይ ካለችው ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር ሁሉም ጉድለቶች እንዳሏቸው የሚያጠራጥር አይደለም ። እነዚህ ፕሮግራሞች አንዳችም እንከን የላቸውም ፣ ሊኖራቸውም አይገባም የሚል ሰው ፡ አብዮት በቲዎሪ ብቻ ፣ በወረቀት ላይ ተነድፎ ብቻ ይደረጋል የሚል የዋህ መሆን አለበት ። ትክክለኛው ፕሮግራም የቱ እንደሆነ ፣ መሟላት ያለበት ጉድለቱ የቱ እንደሆነ የሚያሳየውና እነዚህንም አሟልቶ የሀገራችንን ነፃነት የሚያበሥረው ኃይል የነቃ ፣ የተደራጀና የታጠቀው ሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ብቻ ነው ።



ይህ የሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የረጅም ጊዜ ትግል ያስገኘው አብዮታዊ ፕሮግራም እፍኝ ከማይሞሉ ፀረ—ሕዝብ ኃይሎች በስተቀር የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ክብር ፣ ነፃነትና ጥቅም የሚያረጋግጥ ፕሮግራም ነው ። ነገር ግን ማንም ቢሆን ራሱን ማታለል የለበትም ። የትግል ፍሬ የሆነው ይህ ፕሮግራም ገና ለገና አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚስማማበት ነው በመባሉ ብቻ ከሥራ ላይ አይውልም ። የታወጀው ከረዥም ጊዜ ትግል በኋላ ነው ። ከሥራ ላይ እንዲውል ገና የረዥም ጊዜ መራራ ትግል ይጠይቃል ። ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ገና በሚመጡት ረዥም የትግልና የመሥዋዕትነት ዓመታት የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ፣ ወዝ አደሮች ፣ ጭቁን ወታደሮች ፣ ተራማጅ ምሁራን ፣ ተማሪዎች ፣ መኰንኖች ፣ ነጋዴዎች ፣ አገር ወዳዶች ፣ በጠቅላላው የሰፊው ሕዝብ ወገን የሆነ ኃይሎች በሙሉ ተባብረው በመሰለፍ ገና ለብዙ ዓመታት የሚታገሉበት ፕሮግራም ነው ።

በዚህ የረዥምና የተወሳሰበ የአብዮታዊ ትግል ጉዳና ላይ ይህ ፕሮግራም እንደ አንድ ታላቅ ምዕራፍ የሚቆጠርበት ምክንያት በይዘቱ ብቻ ሳይሆን ከሥራ ላይ የሚውልበትን አማራጭ የሌለው ሳይንሳዊ የትግል ፋና ግልጥልጥ አድርጎ በመቀየሱ ነው ።

ከሁሉ አስቀድሞ ይህ ፕሮግራም ዋስትና ባለው ሁኔታ ሥራ ላይ የሚውለው ዓላማው ጥርት ባለ ሁኔታ ተገልጦ ሲቀመጥ በመሆኑ ገና ለረዥም ጊዜ የትግሉን አቅጣጫ የሚወስነው ዓላማ ጥርት ባለ ሁኔታ ተቀምጦ እናገኘዋለን ።

«ፊውዳሊዝምን ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝምን ከኢትዮጵያ ጨርሶ በመደምሰስ በፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ትብብር አዲሲቱን ሕዝባዊት ኢትዮጵያ መመሥረትና ወደሶሻሊዝም መሸጋገሪያ የሚሆነውን መሠረት መጣል ።

«ለዚህም ዓላማ በወዝ አደሩ መሪነት ፣ በአርሶ አደሩ ተባባሪነት በንዑስ ከበርቴውና በሌሎች ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ደጋፊነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነቱን ፣ እኩልነቱን ፣ አንድነቱን ፣ ሰላምንና ብልጽግናን የሚያረጋግጥበት በየድርሻውም ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለ አንዳች ገደብ ተከብረው በሥራ ላይ የሚውልበት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ማቋቋም »

ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዓላማ ከሀገራችንና ከጊዜው ዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ሳይንሳዊ ትንተና የፈለቀ ዓላማ ነው ። ከሥራ ላይ የመዋሉም ዋስትና ሳይንሳዊ የሆነ የትግል ስልት መቀየስ በመሆኑ ፕሮግራሙ የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፍቱንነታቸውን ያስመሰከረላቸውን የትግል ስልቶች በሙሉ ቀይሶ ያስቀምጣል ።

ይህ ዓላማ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው በሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ብቻ በመሆኑ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ለመማር ፣ ለማስተማር ፣ ለመደራጀትና ለማደራጀት ያላቸውን መብት ያለ አንዳች ገደብ ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ያምናል ።

ይህ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ የተደራጀ መልክ ከሌለው የነፃነቱ ትግል በተደራጁ አድኃርያን ዓመፅና ሤራ ሊፈታ እንደሚችል ያለፈው የኢትዮጵያ ጭቁኖች የትግል ታሪክ ብቻ ሳይሆን የመላ ዓለም ጭቁን ሕዝቦች ተደራጅተው የተቀዳጁት ድል ሆነ ፣ በተበታተነ ትግላቸው የደረሰባቸው ውድቀት እየደጋገመ ያስተማረን ሳይንሳዊ ሐቅ ነው ። ስለሆነም ይህ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል የተደራጀ መልክ እንዲይዝ ለሕዝብ ወገኖች በሙሉ ያልተገደበ የመደራጀት መብት ያበሥራል ።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአብዮቱ ወደፊት መግፋት የቀንደኛ ጠላቶቻችን የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም ፀር የሆኑ ተራማጅ ኃይሎችን መደራጀትና መጠናከር ይጠይቃል ። እነዚህ የተለያዩ ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ለጋራው ትግል ኃይላቸውን

ከማስተባበራቸው በፊት ሁሉም በየፈርጃቸው መደራጀት መቻላቸው ለትብብሩ አስፈላጊውን ጥንካሬ ፣ መተማመንና መፈቃቀድ የሚሰጥ ስልት በመሆኑ የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች አስቀድመው በፓርቲዎችና በሌሎች ልዩ ልዩ ድርጅቶች አማካኝነት መደራጀት እንደሚችሉ ሙሉ በሙሉ ይቀበላል ። ነገር ግን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ያህል የጋራ ጠላቶች ያሉባቸው ተራማጅ ኃይሎች በየፊናቸው በመደራጀታቸውና በመታገላቸው ብቻ ድል መምታት እንደማይችሉና የጋራ ጠላቶቻቸውን በጋራ ትግል ለመደምሰስ የጋራ ግንባር እንደሚያስፈልጋቸው አሁንም የዘመኑ አብዮቶች ታሪክ እየደጋገመ ያሳየን ሐቅ ነው ።

ስለሆነም ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከሥራ ላይ እንዲውል በየፈርጃቸው የሚደራጁት ፓርቲዎች ፣ ሕዝባዊና የሞያ ድርጅቶች ኃይላቸውን በአንድ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ማስተባበር እንዳለባቸው ግልጽ በመሆኑ ፕሮግራሙ ፣

«ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮታችን ነፍቶ ድልን ሊቀዳጅ የሚችለው በመላ በሀገሪቱ የሚገኙ ፀረ—ፊውዳል ፀረ — ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በፓርቲዎቻቸውና በሌሎች ድርጅቶቻቸው አማካኝነት የድርጅት ነፃነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ትግላቸውን የሚያስተባብሩበት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ሲኖራቸው ብቻ እንደሆነ ያረጋግጣል ።

ለአብዮታዊ ድል የጋራ ግንባር ትግል ብቻ አይበቃም ። የማያዳግም ድል እንዲገኝ የወዝ አደሩ የማያወላውልና ቆራጥ ክንድ የግንባሩን አመራር በትግል መጨበጥ ይኖርበታል ። ስለሆነም ይህ የወዝአደሩ ፓርቲ ተቋቁሞና ተጠናክሮ ለተጣለበት ታሪካዊ አደራ ብቁ እንዲሆን « በሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም ታንጾ ትግሉን የሚመራ የወዝአደር ፓርቲ እንዲቋቋም ለሚጣጣሩ አብዮታዊ ቡድኖችና ግለሰቦች በመንግሥት በኩል የማያቋርጥ ድጋፍ መስጠት እንደሚያስፈልግ ፕሮግራሙ ሙሉ በሙሉ ይቀበላል ። ነገር ግን የፊውዳሊዝምና የኢምፔሪያሊዝም መደምሰስ ጉዳይ የአንድ መደብ ብቻ ታሪካዊ አደራ ሳይሆን የተባበሩ ተራማጅ ኃይሎች ተግባር እንደሆነ ግልጽ በመሆኑ ከወዝአደሩ ፓርቲ ሌላ ሌሎች ተራማጅ ፓርቲዎች ለማቋቋም የሚፈልጉ ፀረ—ፊውዳል ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ — ቢሮክራሲያዊ ቡርዧ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ይህንን ማድረግ እንደሚችሉና የመንግሥት ድጋፍና ርዳታም ለነሱም እንደሚሰጥ ያምናል ።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን ሊመታ የሚችለው በተደራጀ ብቻ ሳይሆን በታጠቀ ሕዝባዊ ትግል እንደሚሆን ሳይንሳዊ ትንተና ፣ የሌሎች የዘመኑ አብዮቶች ታሪክና የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አጉልቶ የሚያሳየው ሐቅ ነው ። ፕሮግራሙ ሰፊው ሕዝብ የውስጥና የውጪ ጠላቶቹን ለመደምሰስ መታጠቅ እንደሚኖርበት ከመግለጹም በላይ በፕሮግራሙ መግለጫ ውስጥ አጣዳፊ ተግባሮቻችን በሚለው ርእስ ሥር የሚከተለውን እናገኛለን ።

«የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በዚህ መልክ በፈርጅ በፈርጃቸው እየተደራጁ ወደሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር የሚያመሩት በማያቋርጥ አኳኋን በትግል ውስጥ እየተሳተፉ ለመደራጀት ሲችሉ ነው ። ለዚህም የመንቃቱ ፣ የመደራጀቱና የመታጠቁ የሕዝብ ጠላቶችን የመደምሰሱ ተግባር የማያቋርጥ አብዮታዊ ሂደት አለው » ።

እንግዲህ ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የካቲት ያስነሣው አብታዊ ማዕበል ሲሰክን ሕዝባዊት ኢትዮጵያችን የሚኖራትን ገጽታ የሚያንጸባርቅ ፣ ለዛሬው ደግሞ ለኢትዮጵያ ጭቁኖች የጋራ ትግል መሰብሰቢያና ማስተባበሪያ ሰንደቅ ዓላማ ሆኖ እናገኘዋለን ። ከዚሁ ፕሮግራም ጋር ተያይዞ አብዮታችን ወደመጨረሻው ድል የሚያመራበት የንቃት ፣ የድርጅትና የትጥቅ ጐዳና ያለ አንዳች ማወላወል ግልጥልጥ ብሎ ተጠቁሟል ።

የኢትዮጵያ ተራማጆች ፣ ይህ ፕሮግራም ሊኖረው የሚችለውን ጥቃቅን ጉድለቶች ከዳር ሆነው በመጠቆም አይወስኑም ። ይህ ፕሮግራም በአጠቃላይ ሲታይ የኢትዮጵያ ተራማጆች ከዚህ



ቀደም ለረዥም ጊዜ የታገሉለትና የተሠውለት በሚመጡት ትግል ዓመታት ደግሞ የሚወጡትን መከራና መሥዋዕትነት እየተቀበሉ የሚታገሉለት ሰንደቅ ዓላማቸው ይሆናል ።

ትግሉ ረዥምና የተወሳሰበ ነው ። ነገር ግን ዛሬ የኢትዮጵያ ጭቁኖች በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት በተጐናጸፉት ድል በትግሉና በትርምሱ አቆራርጠው የነገይቱን ሕዝባዊት ኢትዮጵያ መመልከት ጀምረዋል ። ወደዚች የሁላችን የሆነች ነፃ ፣ ኩሩና ጠንካራ ሀገር በምናደርገው የትግልና የመሥዋዕትነት ጉዞ ከእንግዲህ ሊገታን የሚችል ኃይል ከፀሐይ በታች የለም ። እናሸንፋለን ።

**ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።**

**« አብዮታዊት ኢትዮጵያ »**